# ትንቢተ ናሆም

## መግቢያ

### ጸሐፊው

ይህ መጽሐፍ ናሆም ያየውን ራእይ የያዘ ነው (1፥1)፤ ናሆም የስሙ ትርጒም "መጽናናት" ማለት ሲሆን፣ "እግዚአብሔር ያጽናናል" ወይም "የእግዚአብሔር ማጽናናት" የሚል ትርጒም ካለው ከነህምያ ስም ጋር ይመሳሰላል:: የናሆም መጽሐፍ መሪ ሐሳብ የሆነው የነነዌ ውድቀት፣ ለይሁዳ መጽናናትን የሚያመጣ ነው:: የተወለደበት ከተማ ኤልቆሽ ከመሆኑ በስተቀር ስለ ናሆምም ሆነ ስለተወለደበት ስፍራ ብዙ የሚታወቅ ነገር የለም::

### የተጻፈበት ጊዜ

ጸሐፊው በ663 ዓ.ቅ.ክ የተፈጸመው የኖእ አሞን ውድቀት ያለፈ መሆኑን ይናገራል (3፥8-10):: ናሆም በሦስቱም የመጽሐፉ ምዕራፎች ውስጥ የተነበየው በ612 ስለ ተፈጸመው ስለ ነነዌ ውድቀት ስለ ሆነ ትንቢቱ የተነገረው በ663 እና በ612 ዓ.ቅ.ክ ባለው ጊዜ ውስጥ ሊሆን ይችላል:: ነቢዩ በዚሁ መጽሐፉ የነነዌ ውድቀት በደጅ እንደ ሆነ ስለሚናገር (2፥1፤ 3፥14:19)፣ ጊዜው ምናልባት ወደ ምእተ ዓመቱ ማብቂያ ገደማ ሳይሆን አይቀርም:: በዚህ መሠረት ናሆም የኖረው በኢዮስያስ ዘመነ መንግሥት፣ ሶፎንያስና ወጣቱ ኤርምያስ በነበሩበት ጊዜ እንደሆነ መገመት ይቻላል::

### ታሪካዊ ዳራው

በም 1፥1 ላይ ነነዌ ተብላ የተጠቀሰችው አሦር፣ በ722-721 ዓ.ቅ.ክ ሰማርያን ስለአጠፋች በእስራኤል ሰሜናዊ ግዛት የነበረው ሕዝብ በምርኮ ተወስዶአል፤ በይሁዳ ላይ ከፍተኛ ስጋት የምትፈጥር ሆና ነበር:: አሦራውያን እጅግ ጨካኞች ነበሩ፤ ንጉሦቻቸው ሁልጊዜ በተሸነፉ ሕዝቦች ላይ በሚፈጽሙ አሠቃቂ ቅጣት ይደሰቱ ነበር:: በውጊያ የሚሸነፉትን ሕዝብ ከአገሩ አፈናቅለው ወደ ሌሎች ግዛቶቻቸው በማጋዝ አረመኔያዊ ተግባር በላያቸው መፈጸም የመንግሥት መመሪያቸው ነበር:: የተሸነፉ ከተሞች መሪዎች ከመገደላቸው በፊት፣ እንዲሠቃዩና ዘግናኝ በሆነ ሁኔታ አካላቸው እንዲቈራረጥ ይደረግ ነበር:: (የ3፥3 ማብ ይመ)::

ንጉሥ ሰናክሬም በ700 በዓ.ቅ.ክ፣ ነነዌ የአሦር ግዛት ዋና ከተማ እንድትሆን አደረገ፤ በ612 እስከጠፋችበት ጊዜ ድረስ ዋና ከተማ እንደሆነች ቈይታለች:: ቀደም ሲል ከተማዋ እንደምትጠፋ ዮናስ አስታውቆ ነበር (ዮና 3፥4)፤ ነገር ግን ሕዝቡ ንስሓ በመግባቱ፣ ሊደርስባት የነበረው ጥፋት ለጊዜው ቀርቶአል:: በኋላ ግን ነነዌ ብዙም ሳትቈይ ከቀድሞው በባሰ ሁኔታ ወደ ክፋቷ፣ ወደ ጭከናዋና ወደ ትዕቢቷ ተመለሰች:: በታላቁ የአሦር መሪ በአሰናፈር ዘመነ መንግሥት (669-627) ክፋቷ ከፍተኛ ደረጃ ላይ ደረሰ:: ንጉሡ ከሞተ በኋላም ነነዌ እስከ ወደቀችበት (612) ድረስ አሦር የነበራት ኀይልና ዝና እያሽቈለቈለ መጣ (የ1፥14፤2፥1 ማብ ይመ)::

### የመጽሐፉ ተደራስያን

በመጽሐፉ ውስጥ የተጠቀሱት አንዳንድ ቃላት ይሁዳን የሚመለከት ሲሆን (1፥12-13:15 ይመ)፣ አብዛኛው ግን ለነነዌ (1፥11:14፤2፥1:13፤ 3፥5-17:19) ወይም ለንጉሥዋ (3፥18) የተጻፈ ነው:: ይሁን እንጂ መጽሐፉን የሚያነቡት የይሁዳ ሰዎች ነበሩ::

### ሥነ ጽሑፋዊ ዘዬው

የጽሑፉ ይዘት በፍርድ ላይ አጽንዖት የሚያደርግ ሲሆን፣ ለዚህም ትክክለኛ አገላለጽና ምርጥ ቃላት እንደዚሁም ጥልቅ ስሜት፣ ጠንካራ እይታና ድምፀት ተጠቅሞአል:: ቋንቋው ቅኔያዊ ሲሆን፣ ብዙ ተለዋዋጭና ተነጻጻሪ ዘይቤዎችን፣ ሥዕላዊ ቃላትን፣ የመደጋገም ሥልትንና በርካታ አጫጭር ሐረጎችን ያካተተ ነው::

### ከትምህርተ መለኮት አንጻር ያሉ መሪ ሐሳቦች

የመጽሐፉ ማእከላዊ ሐሳብ በነነዌ ላይ ስለሚፈጸመው የእግዚአብሔር ፍርድ ሲሆን፣ ይህም ግፍና ጭካኔ፣ ክፋትና ጣዖትን ማምለክ ከተሞላበት አድራጐቷ የተነሣ ነው፤ መልእክቱም የሚደመደመው በከተማዋ መጥፋት ነው::

በሮሜ 11፥22 ላይ እንደተጠቀሰው እግዚአብሔር ቸር ብቻ ሳይሆን ጨካኝም ነው:: በትንቢተ ናሆም መጽሐፍ መሠረት እግዚአብሔር ለቍጣ የዘገየና (1፥3) ለሚታመኑበት መሸሸጊያ ብቻ ሳይሆን (1፥7)፣ ኀጢአተኛውን ሳይቀጣ የማይተዉም (1፥3) አምላክ ነው:: በስተ መጨረሻ የእግዚአብሔር ጽድቅና ትክክለኛ መንግሥት አሸናፊ ይሆናል፤ አሦር እንደ ወደቀች ሁሉ በክፋት ላይ የተመሠረተና ጨካኝ መንግሥትም በመጨረሻ መውደቁ የማይቀር ነው:: ከዚህም በተጨማሪ እግዚአብሔር የታሪክና የመንግሥታት ሁሉ ጌታ በፍጥረተ ዓለም ላይ ሉዐላዊ አምላክ መሆኑን ናሆም ይናገራል::

### አስተዋፅኦ

1. ርእስ (1፥1)

2. በነነዌ ላይ የሚፈርደው ዳኛ (1፥2-15)
    ሀ. የእግዚአብሔር ቸርነትና ጭካኔ (1፥2-8)
    ለ. የነነዌ መጣልና የይሁዳ ደስታ (1፥9-15)
3. በነነዌ ላይ የተሰጠው ፍርድ (ም2)
    ሀ. የነነዌ መከበብ (2፥1-10)
    ለ. ነነዌ ባድማ መሆንዋ ቀድሞ ከነበራት ክብር ጋር ሲነጻጸር (2፥11-13)
4. የነነዌ ሙሉ በሙሉ መጥፋት (ም3)
    ሀ. የነነዌ ኀጢአት (3፥1-4)
    ለ. በነነዌ ላይ የደረሰው ጥፋት (3፥5-19)

1 ስለ ነነዌ ጥፋት የተነገረ ንግር፤ የኤልቆሻ
ዊው የናሆም የራእዩ መጽሐፍ ይህ ነው፤

**በነነዌ ላይ የተገለጠ የእግዚአብሔር ቍጣ**

2 *እግዚአብሔር* ቀናተኛና ተበቃይ አምላክ ነው፤
*እግዚአብሔር* የሚበቀል፣ በመዓትም
የተሞላ ነው።
*እግዚአብሔር* ባላጋራዎቹን ይበቀላል፤
በጠላቶቹም ላይ ቍጣውን ያመጣል
3 *እግዚአብሔር* ለቍጣ የዘገየ በኀይሉም
ታላቅ ነው፤
*እግዚአብሔር* በደለኛውን ሳይቀጣ አያልፍም፤
መንገዱ በዐውሎ ነፋስና በማዕበል ውስጥ ነው፤
ደመናም የእግሩ ትቢያ ነው።
4 ባሕርን ይገሥጻል፤ ያደርቀዋልም፤
ወንዞችን ሁሉ ያደርቃል።
ባሳንና ቀርሜሎስ ጠውልገዋል፤
የሊባኖስም አበቦች ረግፈዋል።
5 ተራሮች በፊቱ ታወኩ፤
ኰረብቶችም ቀለጡ።
ምድር በፊቱ፣
ዓለምና በውስጧ የሚኖሩት ሁሉ ተናወጡ።
6 ቍጣውን ማን ሊቋቋም ይችላል?
ጽኑ ቍጣውንስ ማን ሊሸከም ይችላል?
መዓቱ እንደ እሳት ፈሶአል፤
ዐለቶችም በፊቱ ተሰነጣጥቀዋል።
7 *እግዚአብሔር* መልካም ነው፤
በጭንቅ ጊዜም መሸሸጊያ ነው።
ለሚታመኑበት ይጠነቀቅላቸዋል፤
8 ነነዌን ግን፣
በሚያጥለቀልቅ ጐርፍ ያጠፋታል፤
ጠላቶቹንም ወደ ጨለማ ያሳድዳቸዋል።

1፥1 ዘፍ10፥11፤ኢሳ 1፥1፤13፥1፤19፥1፤ ኤር 23፥33፡34፤ 50፥18፤ ናሆ2፥8፤ 3፥7
1፥2 ዘፍ4፥24፤ዘፀ 20፥5፤ዘዳ7፥10፤32፥41፤ መዝ94፥1
1፥3 ዘፀ14፥21፤ 34፥7፤ 2ሳሙ22፥10፤2ነገ2፥1፤ነሆ9፥17፤መዝ50፥3፤ 104፥3
1፥4 ዘፀ14፥22፤ 2ሳሙ 22፥16፤ኢሳ 33፥9
1፥5 ዘፀ19፥18፤ኢ ዮ9፥6፤ሕዝ38፥20፤ ኢል2፥10፤ሚክ1፥4
1፥6 1ነገ19፥11፤ መዝ76፥7፤130፥3፤ ኢሳ5፥24-25፤ 42፥25፤ኤር10፥10፤ሕ ዝ22፥14
1፥7 መዝ1፥6፤22፥9፤ ኤር17፥17፤33፥11
1፥8 ኢሳ8፥7፤ ዳን9፥26
1፥9 ሆሴ7፥15
1፥10 2ሳሙ23፥6፤ ኢሳ5፥24፤49፥26፤ ሚል4፥1
1፥12 ኢሳ10፥34፤ 54፥6-8፤ሰቆ3፥31-32
1፥13 ኢዮ12፥18፤ መዝ107፥14፤ኢሳ9፥4
1፥14 ኢሳ14፥22፤ ኤር28፥8፤ሕዝ32፥ 22-23፤ሚክ5፥13
1፥15 ዘሌ23፥2-4፤ኢሳ 40፥9፤52፥1፡7፤ሐሥ 10፥36፤ሮሜ10፥15

9 *በእግዚአብሔር* ላይ ምንም ቢያሤሩ[ሀ]፣
እርሱ ያጠፋዋል፤
መከራም ዳግመኛ አይነሣም።
10 በእሾህ ይጠላለፋሉ፤
በወይን ጠጃቸውም ይሰክራሉ፤
እሳትም እንደ ገለባ[ለ] ይበላቸዋል።
11 ነነዌ ሆይ፤ *በእግዚአብሔር* ላይ የሚያሤር፣
ክፋትንም የሚመክር፣
ከአንቺ ዘንድ ወጥቶአል።
12 *እግዚአብሔር* እንዲህ ይላል፤
"ምንም ኀይለኞችና ብዙዎች ቢሆኑም፣
ይቈረጣሉ፤ ይጠፋሉም።
ይሁዳ ሆይ፤ ከዚህ በፊት ባስጨንቅህም፣
ከእንግዲህ አላስጨንቅህም።
13 አሁንም ቀንበራቸውን ከዐንገትህ ላይ
አንሥቼ እሰብራለሁ፤
የታሰርህበትንም ሰንሰለት በጥሼ
እጥላለሁ።"
14 አንቺ ነነዌ፤ *እግዚአብሔር* ስለ አንቺ
እንዲህ ብሎ አዞአል፤
"ስም የሚያስጠራ ትውልድ አይኖራችሁም፤
በአማልክቶቻችሁ ቤት ያሉትን፣
የተቀረጹትን ምስሎችና ቀልጠው
የተሠሩትን ጣዖታት እደመስሳለሁ፤
መቃብሪያህን እምስልሃለሁ፤
አንተ ክፉ ነህና።
15 እነሆ፤ የምሥራች የሚያመጣውን፣
ሰላምን የሚያውጀው ሰው እግር፣
በተራሮች ላይ ነው፤

ሀ9 *በእግዚአብሔር ላይ የምታሤሩት ምንድን ነው? የሚሉ አሉ*
ለ10 የዕብራይስጡ ትርጕም በትክክል አይታወቅም።

*1፥1፤* የመጽሐፉ ርእስ የተጠቀሰበት ነው። *ንግር፤* የኢሳ 13፥1 ማብ ይመ። *ነነዌ፤* ከመግቢያው "ታሪካዊ ዳራ" የሚለውን ይመ፤ እንዲሁም የዮና 1፥2፤ 3፥3፥ማብ ይመ፤ በዚህ ላይ ዋናው ከተማ ነነዌ፣ መላውን የአሦርን ግዛት ይወክላል። *የራእዩ፤* የኢሳ1፥1 ማብ ይመ። *የኤልቆሻዊው የናሆም፤* ከመግቢያው "ጸሓፊው" የሚለውን ይመ።

*1፥2-3፤* የኪዳኑ ስም የሆነው ያህዌ (*እግዚአብሔር*) በዚህ ስፍራ አጽንዖት ተሰጥቶታል።

1፥2 *ቀናተኛና፤* የዘፀ20፥5 ማብ ይመ። *ተበቃይ...የሚበቀል...ይበቀላል፤* እግዚአብሔር እርሱንና መንግሥቱን የሚቃወሙትን ሁሉ በጽድቅ ይፈርድባቸዋል። ተደጋግሞ መጠቀሱ፣ አጽንዖትን እንደተሰጠው የሚያሳይ ነው።

1፥3 *በደለኛውን፤* እንደ ነነዌ ዐይነቱን ማለት ነው። *በዐውሎ ነፋስና በማዕበል...ደመናም፤* የመዝ 18፥7-15፤ 68፥4፤ 77፥ 16-19፤104፥3-4 ማብ ይመ።

1፥4 *ባሕርን ይገሥጻል፤ ያደርቀዋልም፤* ቀይ ባሕርን በተሻገሩ ጊዜ እንዳደረገው ዐይነት ማለት ነው (ዘፀ14)። *ወንዞችን ሁሉ ያደርቃል፤* ዮርዳኖስን በተሻገሩ ጊዜ እንዳደረገው ዐይነት ነው (ኢሱ3)። *ባሳንና፤* በለም የግጦሽ መሬት የታወቀ ነው (አሞ4፥1)። *ቀርሜሎስ፤* በወይን ዕርሻ የታወቀ ነው(አሞ1፥2)። *የሊባኖስም፤* በምርጥ ዛፎቹ የታወቀ ነው (ሕዝ31፥16)። ማሕ 7፥5፤ የኢሳ 2፥13፤33፥9፤35፥2፤የአሞ4፥1 ማብ ይመ። ይሁን እንጂ እነዚህ ሁሉ በእግዚአብሔር ቃል ይደርቃሉ።

1፥5 *ተራሮች...ኰረብቶችም...ምድር...ዓለምና፤* የጽናትና የቋሚ ነገር ምልክቶች ናቸው።

1፥6 *ማን ሊቋቋም ይችላል?...ማን ሊሸከም ይችላል?* መልስ ዐዘል ጥያቄዎች ናቸው። ተራሮች በእግዚአብሔር ፊት ሲንቀጠቀጡ (ቍ5) አልጉዳም ብሎ የሚያስብ የሰው ልጅ ማን ነው?፤ ከሮሜ2፥3-5 ጋር ያነጻጽሩ።

1፥7 *ለሚታመኑበት፤* እንደ ይሁዳ ለማለት ነው።

1፥8 *በሚያጥለቀልቅ ጐርፍ፤* ወራሪውን ኀይል በትእምርት የሚገልጽ ነው (ኢሳ8፥7-8 ይመ)። *ያጠፋታል...ጨለማ፤* በ612 ዓ.ቅ.ክ. ያ ጥፋት በነነዌ ላይ ደረሰ፤ ጨለማም ዋጣት። በዮናስ አገልግሎት አማካይነት ነነዌ ቀደም ሲል የእግዚአብሔርን ብርሃን አግኝታ ነበር ኋላ ግን ገፋችው፤ ውጤቱም የጨለማን ፍርድ አስከተለ።

1፥9 *ቢያሤሩ፤* የቍ11 ማብ ይመ። *መከራም ዳግመኛ አይነሣም፤* እግዚአብሔር አሦራውያን በአይሁዳውያን ላይ ለሁለተኛ ጊዜ ድል እንዲያገኙ አልፈቀደላቸውም፤ የመጀመሪያው የሰሜኑ መንግሥት የሰማርያ መውደቅ ነበር (722-721 ዓ.ቅ.ክ.)፤ ሰናክሬም በ701 ያደረገው ወረራ ፍጹም ድልን አላስገኘም (2ነገ18፥13-19፥37፤ኢሳ 36-37 ይመ)።

1፥10 *በወይን ጠጃቸውም ይሰክራሉ፤* 3፥11 እና ማብ ይመ።

1፥11 *የሚያሤር፤* ምናልባት የመጨረሻው የአሦር ታላቁ ንጉሥ ነገሥትና በምዕራብ በኩል ዘምቶ ግብፅን የገዛውና ንጉሥ ምናሴም እንዲገብርለት ያደረገው የአሦር ንጉሥ አሹር ባኒፓል ሳይሆን አይቀርም(ከ669-627 ዓ.ቅ.ክ.)፤ 2ዜና33፥11-13 ይመ።

1፥12 ቢሆኑም (እነርሱ)፤ አሦራውያንን ማለት ነው። *ባስጨንቅህም፤* እግዚአብሔር በአካዝ ዘመን (ኢሳ10፥5)እንደገናም በምናሴ ዘመን፣ ቃል ኪዳኑን ያፈረሰውን ሕዝብ ለመቅጣት አሦራውያንን የቍጣው በትር አድርጎ ተጠቅሞባቸዋል።

1፥13 *ቀንበራቸውን...እሰብራለሁ፤* ይሁዳ የአሦር ገባር ሆና ነበር፣ ስለዚህ ያ ቀንበር ይሰበራል።

1፥14 *መቃብሪያህን እምስልሃለሁ፤* እግዚአብሔር ባቢሎናውያንን፣ ሜዶናውያንንና እስኩቴያንስን የነነዌን መቃብር እንዲቈፍሩ በ612 ዓ.ቅ.ክ. ተጠቅሞባቸዋል፤ የዚህን ትንቢት ፍጻሜ በተመለከተ ሕዝ32፥22-23 ይመ።

1፥15 *በተራሮች፤* የይሁዳና የኢየሩሳሌም ናቸው። *የምሥራች የሚያመጣውን.. ሰው እግር፤* ይህ ጥቅስ ትድግናን በሚያሳዩ ብዙ ዐውዶች ውስጥ ተግባራዊ የሚሆን መርሕን ያመለክታል። በዚህ ስፍራ የተገለጸው ትድግና ግን ከአሦራውያን

ይሁዳ ሆይ፤ በዓላትህን አክብር፤
ስእለትህንም ፈጽም፤
ከእንግዲህ ክፉዎች አይወሩህም፤
እነርሱም ፈጽመው ይጠፋሉ።

## የነነዌ አወዳደቅ

2 ነነዌ ሆይ፤ አጥቂ መጥቶብሻል፤
ምሽግሽን ጠብቂ፤
መንገድሽን ሰልዪ፤
ወገብሽን ታጠቂ፤
ኀይልሽን ሁሉ አሰባስቢ።

2 አጥፊዎች ባድማ ቢያደርጓቸውም፣
የወይን ተክል ቦታቸውን
ቢያጠፉባቸውም፣
እንደ እስራኤል ክብር ሁሉ፣
እግዚአብሔር የያዕቆብንም ክብር
ይመልሳል።

3 የወታደሮቹ ጋሻ ቀይ ነው፤
ተዋጊዎቹ ቀይ ልብስ ለብሰዋል፤
ዝግጁ በሆኑበት ቀን፣
የሠረገሎቹ ብረት ያብረቀርቃል፤
የጦሩ ዘንግ ይወዛወዛል።
4 ሠረገሎች በአደባባይ ወዲያ ወዲህ
ይከንፋሉ፤
በመንገዶችም ላይ ይርመሰመሳሉ፤
የሚንበለበል ፋና ይመስላሉ፤
እንደ መብረቅም ይወረወራሉ።

5 ምርጥ ተዋጊዎቹን ይጠራል፤
ዳሩ ግን መንገድ ላይ ይሰናከላሉ፤
ወደ ከተማዪቱ ቅጥር ይሮጣሉ፤
መከላከያ ጋሻውም በቦታው አለ።
6 የወንዙ በር ወለል ብሎ ተከፈተ፤
ቤተ መንግሥቱም ወደቀ።
7 ከተማዪቱ መማረኳና መወሰዷ እንደ
ማይቀር፣
አስቀድሞ ተነግሮአል¬፤
ሴቶች ባሪያዎቿ እንደ ርግብ ያለቅሳሉ፤
ደረታቸውንም ይደቃሉ።
8 ነነዌ እንደ ኵሬ ናት፤
ውሃዋም ይደርቃል፤
"ቁም! ቁም!" ብለው ይጮኻሉ፤
ነገር ግን ወደ ኋላ የሚመለስ የለም።
9 ብሩን ዝረፉ፤
ወርቁን ንጠቁ፤
በየግምጃ ቤቱ ያለው፤
የተከማቸውም ሀብት ስፍር ቍጥር
የለውም።
10 ተበዝብዛለች፤ ተዘርፋለች፤ ተራቍታለች።
ልብ ቀልጦአል፤ ጒልበት ተብረክርኮአል፤
ሰውነት ተንቀጥቅጦአል፤ ፊት ሁሉ
ገርጥቶአል።

11 አሁን ታዲያ የአንበሶቹ ዋሻ፣
ደቦሎቻቸውን ያበሉበት
ወንዱና ሴቷ አንበሳ የሄዱበት፣
ግልገሎችም ሳይፈሩ የተሰማሩበት ቦታ
ወዴት ነው?

2፥1 ኢር51፥20
2፥2 ኢሳ60፥15፤ ሕዝ 37፥23
2፥3 ሕዝ23፥14-15
2፥4 ኢር4፥13፤ሕዝ 23፥24
2፥5 ኢር46፥12
2፥6 ኢሳ45፥1፤ ናሆ3፥13
2፥7 ዘፍ8፥8፤ኢሳ 32፥12፤59፥11
2፥10 ኢሱ2፥11፤ 7፥5፤ኢሳ29፥22
2፥11 ኢሳ5፥29

*3 የዕብራይስጡ ትርጒም ከዚህ ጋር ይስማማል፤ የሰብዓ ሊቃናቱና የሱርስቱ ቅጆች ግን ፈረሰኞች ይፈጥናሉ ይላሉ።
¬7 የዕብራይስጡ ቃል ትርጒም በትክክል አይታወቅም።

ጥቃት ነጻ መውጣትን ነው፤ በኢሳ52፥7 ከባቢሎናውያን ምርኮ ነጻ መውጣትን፣ ሲያመለክት በሮሜ 10፥15 ደግሞ በክርስቶስ ወንጌል ከኀጢአት ነጻ መውጣትን ያመለክታል። *በዓላትህን አክብር፤* ነጻ ከመውጣት ደስታ የተነሣ ነው። *ስእለትህንም ፈጽም፤* በጭንቅህ ጊዜ የተሳልከውን ለማለት ነው፤ የመዝ7፥17 ማብ ይመ። *ከእንግዲህ ክፉዎች አይወሩህም፤* በምናሴ ዘመን የነበረው የአሦራውያን ወረራ የመጨረሻው ነበር። *ክፉዎች፤* የዘዳ13፥13 ማብ ይመ። *ፈጽመው ይጠፋሉ፤* ነነዌ በ612 በወደቀች ጊዜ ተፈጸመ (የቍ14ማብ ይመ)።

2፥1 *አጥቂ፤* በተለይ በሲያክሳሬስ አገዛዝ እንዲሁም በናቦፓላሳር አገዛዝ ሥር ያሉትን የባቢሎናውያን አጋር የሆኑትን ሜዶናውያንንና ሰካይትያንን ያመለክታል። *ምሽግሽን "ጠብቂ"*.. *"ኀይልሽን" ሁሉ አሰባስቢ፤* ምናልባት ሥላቅ ያለበት ምፀታዊ አነጋገር ሳይሆን አይቀርም። *መንገድሽን፤* ጠላት የሚመጣበትን ያመለክታል።

2፥2 *እንደ እስራኤል ክብር...የያዕቆብንም ክብር ይመልሳል፤* ተከፍሎ የነበረው ሕዝብ ሁሉ ተመልሶ አንድ ይሆናል።

2፥3 *የወታደሮቹ፤* አጥቂዎቹ (ቍ1) ወይም የነነዌ ሰዎች ሊሆኑ ይችላሉ። *ቀይ፤* የጋሻዎቹ ቀለም ወይም በላያቸው ላይ ያለው ደም ወይም ላያቸው ላይ ያለው የፀሐይ ነጸብራቅ ሊሆን ይችላል። *ይወዛወዛል፤* ለውጊያ ዝግጁ መሆኑን የሚያመለክት ነው።

2፥4 *ሠረገሎች... ይከንፋሉ፤* ይህም (1) የአሦርን የጦር ሠረገሎችና አሦራውያን ራሳቸውን ለመከላከል ሲሉ ታይቶ በማይታወቅ ሁኔታ የደመ ነፍስ ጥድፊያ ማድረጋቸውን ያመለክታል፤ ወይም (2) ነነዌን የወረሩ ሠረገሎችን ሊያሳዩ ይችላል። የነነዌ ወራሪዎችን ሠረገሎች ነው።

2፥5 *ይጠራል (እርሱ)፤* ምናልባት የአሦር ንጉሥ ሊሆን ይችላል። *ወደ ከተማይቱ ቅጥር፤* 12.8 ኪሎሜትር ርዝመትና 15 መግቢያ በሮች ወዳሉት ወደ ነነዌ ቅጥር ከመድረሱ በፊት 45 ሜትር ስፋት ያለው በውሃ የተሞላ ጥልቅ ጒድጓድ አለ። ቅጥር ማፍረሻ ግንዲላዎችም ወደ ላይ ተነሥተው ነበር። *መከላከያ ጋሻውም፤* ተጠቂዎች የሚይዙት ሲሆን በቅጥሩ ላይ ያሉት ወታደሮች ከወራሪዎች የሚወረወርባቸውን ቀስትና ድንጋይ የሚመክቱበት በቈዳ የተለበጠ ጋሻ ነው።

2፥6 *የወንዙ በር፤* ምናልባት በከተማው አድርጎ ወደ ጤግሮስ ወንዝ በሚፈሰው በኮሸር ወንዝ ላይ የተሠሩ ግድቦች ናቸው። እነርሱም ቀድሞ በቦታው ላይ ያሉ ወይም የወንዙን ውሃ ለማኁልበት በፍጥነት የተሠሩ ሲሆን፤ ቅጥሩን እንዲያፈራርሱ ድንገት ይለቀቃሉ። *ወደቀ፤* የባቢሎናውያንን ዜና መዋዕል የጻፈ አንድ የጥንት ታሪክ ጸሓፊ የቅጥሩን ክፊል፣ ጐርፍ ይዞት እንደ ሄደና ወራሪው ኀይል በቀላሉ ወደ ከተማይቱ እንደገባ ተናግሮአል።

2፥7 *ሴቶች ባሪያዎቿ፤* ምናልባት የንግድ ቦታቸውና ጣዖታቸው የፈራረሱባቸው የቤተ ጣዖት ዘሙት አዳሪዎች ሳይሆኑ አይቀርም።

2፥8 *እንደ ኵሬ...ውሃዋም ይደርቃል፤* አንዳንዶች ይህ ጤግሮስንና በከተማዪቱ ዙሪያ የተወሰነ ክፍል የሚፈሱትን ትናንሽ ወንዞች እንዲሁም ከተማዪቷ ፈጽሞ የማትበገር እንድትሆን የሚያደርጓትን የግድቦቹን አሠራር ያመለክታል ብለው ያስባሉ። ሌሎች ደግሞ አባባሉን በቁሙ ሳይተረጒሙ ውሃ ከኵሬ እንጥፍጥፍ ብሎ እንደሚፈስ ጥርግርግ ብለው የሚሸሹትን የነነዌን ሰዎች ያመለክታል ይላሉ።

*2፥9፤* የወራሪዎችን ጩኸት ያመለክታል።

2፥10 *ተበዝብዛለች፤ ተዘርፋለች፤ ተራቍታለች፤* በዕብራይስጥ እነዚህ ሦስቱ ቃሎች በአንድ ቃል ይወከላሉ። የባቢሎናውያን ዜና መዋዕል፣ ወራሪዎች አያሌ ንብረት ዘርፈው እንደወሰዱ ያመለክታል። *ልብ ቀልጦአል፤* ጨካኞቹና ባለጌዎቹ የነነዌ ሰዎች በፍርሀት የሚይዙትንና የሚጨብጡትን አጡ።

*2፥11-13፤* ናሆም ዘይቤአዊ በሆነ አገላለጽ የነነዌን ከተማ የቀድሞ ክብርና ኀይል፣ ምፀታዊ በሆነ አነጋገር ከውድመቷና ከጥፋትዋ ጋር ያነጻጽራል።

2፥11 *ወንዱና ሴቷ አንበሳ፤* ከኢሳ 5፥29፤ ከኢር4፥7፤ ከሆሴ 5፥14፤ ከሚክ 5፥8 ጋር ያነጻጽሩ። የአሦር ነገሥታት ስግብግብና ዘራፊዎች ከመሆናቸው የተነሣ እንዲሁም የነነዌ ከተማ በአንበሳ ምስል ቅርጻ ቅርጾች በመሞላቷ፣ አሦር በአንበሳ መመሰሏ ትክክለኛ ነው።

[12]አንበሳው ለግልገሎቹ የሚበቃውን ያህል
ገደለ፤
ለእንስቶቹም ዐንቆ ገደለላቸው፤
የገደለውን በማረፊያ ቦታው፣
የነጠቀውንም በዋሻው ሞልቶታል።
[13]የሰራዊት ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ
ይላል፤
"በእናንተ ላይ ተነሥቼባችኋለሁ፤
ሠረገሎቻችሁን አቃጥዬ አጨሳለሁ፤
ደቦል አንበሶቻችሁን ሰይፍ ይበላል፤
የምትበሉትን በምድር ላይ
አልተውላችሁም፤
የመልእክተኞቻችሁም ድምፅ፣
ከእንግዲህ ወዲያ አይሰማም።"

**ለነነዌ**

**3** ለደም ከተማ ወዮላት!
ሐሰት፣
ዘረፋም ሞልቶባታል፤
ብዝበዛዋ ተግዞ አያልቅም።
[2]የጅራፍ ድምፅ፣
የመንኰራኵር ኳኳቴ፣
የፈጣን ፈረስ ኰቴ፣
የሠረገሎች ድምፅ ተሰምቶአል
[3]ፈረሰኛው ይጋልባል፤
ሰይፍ ይንቦገቦጋል፤
ጦር ያብረቀርቃል፤
የሞተው ብዙ ነው፤
ሬሳ በሬሳ ሆኖአል፤
ስፍር ቍጥር የለውም፤
መተላለፊያ አልተገኘም።
[4]ይህ ሁሉ የሆነው ቅጥ ባጣች፣
አሳሳችና መተተኛ በሆነች ዘማዊት
ምክንያት ነው፤
እርሷም በዝሙቷ አሕዛብን፣
በጥንቈላዋም ሕዝቦችን ባሪያ ያደረገች
ናት።
[5]የሰራዊት ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ
ይላል፤
"እኔ በጠላትነት ተነሥቼብሻለሁ፤
ቀሚስሽን እስከ ፊትሽ እገልበዋለሁ፤
ዕርቃንሽን ለአሕዛብ፣
ኀፍረትሽንም ለነገሥታት አሳያለሁ።
[6]ቍሻሻ እደፋብሻለሁ፤
እንቅሻለሁ፤
ማላገጫም አደርግሻለሁ።
[7]የሚያዩሽ ሁሉ ከአንቺ እየሸሹ፣
'ነነዌ ፈራርሳለች፤ ማን ያለቅስላታል?'
ይላሉ፤
የሚያጽናናሽንስ ከወዴት አገኛለሁ?"
[8]አንቺ በዐባይ ወንዝ አጠገብ ካለችው፣
በውሃ ከተከበበችው፣
ከኖእ አሞን* ትበልጫለሽን?
ወንዙ መከላከያዋ፣
ውሃውም ቅጥሯ ነው።
[9]ኢትዮጵያና ግብፅ ወሰን የለሽ ኀይሏ
ናቸው፤
ፉጥና ሊቢያም ረዳቶቿ ነበሩ።
[10]ይሁን እንጂ በምርኮ ተወሰደች፤
ተሰዳም ሄደች።
በየመንገዱ ማእዘን ላይ፣
ሕፃናቷ ተፈጠፈጡ፤
በመሳፍንቷ ላይ ዕጣ ተጣለ፤
ታላላቅ ሰዎቿ ሁሉ በሰንሰለት ታሰሩ።
[11]አንቺ ደግሞ ትሰክሪያለሽ፤
ትደበቂያለሽ፣
ከጠላትም መሸሸጊያ ትፈልጊያለሽ።
[12]ምሽጎችሽ ሁሉ ሊበሉ እንደ ደረሱ
የመጀመሪያ በለስ ፍሬ ናቸው፤
በሚወዛወዙበት ጊዜ፣
ፍሬዎቹ በበላተኛው አፍ ውስጥ
ይወድቃሉ።

*8 አንዳንዶች *ቴብስ* ይላሉ።

2፥12 ኢሳ37፥18፤ ኤር 4፥7፤51፥34
2፥13 2ሳሙ2፥26፤ መዝ46፥9፤ኢሳ 10፥5-13፤ኤር21፥13፤ሚክ5፥6፤ናሆ3፥5
3፥1 መዝ12፥2፤ሕዝ 22፥2፤ሚክ3፥10
3፥3 2ነገ19፥35፤ ኢሳ 34፥3፤ኤር47፥3
3፥4 ኢሳ23፥17፤ 47፥9፤ሕዝ16፥25-29
3፥5 ኢሳ20፥4፤ 47፥3፤ ኤር13፥22፤ ናሆ2፥13
3፥6 ዘዐ29፥14፤ 1ሳሙ2፥30፤ኢዮ9፥31፤ኢሳ14፥16፤ኤር 51፥37
3፥7 ኢዮ3፥14፤ኢሳ 13፥14፤31፥9፤51፥19፤ ኤር15፥5፤ናሆ1፥1
3፥8 ኢሳ19፥6-9፤ ኤር46፥25፤አሞ6፥2
3፥9 ዘፍ10፥6፤ 2ዜና12፥3፤ሕዝ27፥10፤30፥5
3፥10 2ነገ8፥12፤ ኢዮ6፥27፤ኢሳ 13፥16፤20፥4፤ኤር 40፥1፤ሕዝ24፥6፤ሆሴ 13፥16
3፥11 ኢሳ2፥10፤ 49፥26፤ናሆ2፥1
3፥12 ማሕ2፥13፤ ኢሳ28፥4

2፥12 *የገደለውን በማረፊያ..ሞልቶታል፤* ነነዌ ከተማ ከተሸነፉ አገሮች በጦርነት በተገኘ ምርኮ ተሞልታ ነበር።

2፥13 *አቃጥዬ አጨሳለሁ፤* የነነዌ ውድቀት እውን የሚሆነው በተፈጥሮ ኀይል ወይም በሚወዳት ኀያላን መንግሥታት አማካይነት ሳይሆን፣ በእግዚአብሔር ኀይል የሚፈጸም ነው። ነነዌ ፍርድ ፊት ቀርባ በደለኛ ሆና ስለተገኘች፣ ትጠፋ ዘንድ ተፈርዶባታል። *ድምፅ፣ ከእንግዲህ ወዲያ አይሰማም፤* ይህንኑ ትንቢት ታሪክ አረጋግጦታል።

3፥1 *ለደም ከተማ፤* ነነዌ ያሸነፈቻቸውን ጠላቶች ጨፍጭፋ እንደምትገድል የታወቀ ነው። አሦራውያን በርኅራኄ ቢስነታቸው፣ በጨካኝነታቸውና በዐረመኔ ድርጊቶቻቸው የታወቁ ነበሩ፤ የማረኳቸውን ብዙዎችን ሰይፈዋል፤ በጦር ወግተዋል ወይም አቃጥለዋል።

3፥3 *ሬሳ በሬሳ ሆኖአል፤* የአሦር ንጉሥ ስልምናሶር ሣልሳዊ በጠላት ከተማ መግቢያ ላይ፣ በተቈረጠ የሰው ራስ ፒራሚድ በማቆም ይኵራራ ነበር። ሌሎች የአሦር ነገሥታት የጠላቶቻቸውን ሬሳ እንደ ግንዲላ በማጋደም በአሸነፉአቸው ከተሞች የቅጥር በሮች ላይ ይከምሩ ነበር። ናሆም ስለ ጨካኞቹ አሦራውያን ያደረገው ገለጻ ተገቢ ነው።

3፥4 *ዘማዊት፤* ምናልባት ዋነኛ የፍቅር አምላክ ተብላ የምትታወቀውን የነነዌን ጣዖት ወይም በአጠቃላይ ከተማዪቱን የሚመለከት ነው። የሀብት ብዛትና የተንደላቀቀ ሕይወት ብዙዎችን ወደ ነነዌ ስቦ ነበር። *መተተኛ...በጥንቈላዋም፤* ዘዳ18፥10 ይመ።

3፥5 *ቀሚስሽን እስከ ፊትሽ እገልበዋለሁ፤* ዝሙት አዳሪዎችና ጋለሞታዎች የሚቀጡት ዐይነት ቅጣት ነው።

*3፥6፤* ነነዌ እንደምትዋረድ ያመለክታል።

3፥7 *ማን?...ከወዴት...?* መልስ አዘል ጥያቄዎች ናቸው፤ ነነዌ የሚራራላት እንደማታገኝ ያመለክታል።

3፥8 *ከኖእ አሞን (ቴብስ)፤* የአሞን ከተማ ወይም የአሞን አምላክ ከተማ ማለት ነው። ቴብስ፤ የላይኛው ግብፅ ታላቂቱ ከተማ ናት። ይዞታዋ ዛሬ በሉክሰርና በከርናክ ከተሞች ግዛት ሥር ነው። በ663 ዓ.ቅ.ክ. ይህች ከተማ በአሦራውያን ተደመሰሰች።

3፥9፤ *ፉጥና፤* የግብፅ አጐራባች ስትሆን፣ ስፍራዋ የት እንደ ሆነ አይታወቅም።

3፥10 *ታላላቅ ሰዎችዋ ሁሉ በሰንሰለት ታሰሩ፤* የአሦር ነገሥታት ብዙ ጊዜ ይህን ያደርጉ ነበር፤ ለምሳሌ አሹርባኒፓል የተባለው የአሦር ንጉሥ ስለያዘው አንድ መሪ ሲናገር፣ በውሻ ሰንሰለት አሰርሁት፣ "ከነነዌ በስተ ምሥራቅ በር በውሻ ቤት አኖርሁት" በማለት ያደረገውን ገልጾአል።

3፥11 *ትሰክሪአለሽ፤* ምናልባት ከእግዚአብሔር የቍጣ ጽዋ ጠጥታ ለማለት ነው።

3፥12 *የመጀመሪያ በለስ ፍሬ፤* ድል አድራጊዎች የነነዌን ብልጥግና ለመዝረፍ ያላቸውን ጕጕት ለማሳየት የገባ ዘይቤአዊ አገላለጽ ነው። *ፍሬዎቹ በበላተኛው አፍ*

13 እነሆ፣ ጭፍሮችሽ፣
ሁሉም ሴቶች ናቸው!
የምድርሽ በሮች፣
ለጠላቶችሽ ወለል ብለው ተከፍተዋል፤
መዝጊያዎቻቸውንም እሳት በልቶአቸዋል::
14 ለከበባው ውሃ ቅጂ፤
መከላከያሽን አጠናክሪ፤
የሸክላውን ዐፈር ፈልጊ፤
ጭቃውን ርገጪ፤
ጡቡንም ሥሪ::
15 በዚያ እሳት ይበላሻል፤
ሰይፍ ይቈርጥሻል፤
እንደ ኵብኵባም ይግጥሻል::
እንደ ኵብኵባ እርቢ፤
እንደ አንበጣም ተባዢ::
16 ከሰማይ ከዋክብት እስኪበልጡ ድረስ፣
የነጋዴዎችሽን ቍጥር አበዛሽ፤
ምድሪቱን ግን እንደ አንበጣ ግጠው
አሟጠጡ፤
ከዚያም በረው ሄዱ::
17 ጠባቂዎችሽ እንደ አንበጣ፣
መኳንንቶችሽም በብርድ ቀን
በቅጥር ሥር እንደሚቀመጥ ኵብኵባ ናቸው፤
ፀሓይ ሲወጣ ግን ይበራሉ፤
የት እንደሚበሩም አይታወቅም::
18 የአሦር ንጉሥ ሆይ፤ እረኞችህ[ሩ]
አንቀላፉ፤
መኳንንትህ ዐርፈው ተኙ፤
ሕዝብህ ሰብሳቢ አጥተው፣
በተራራ ላይ ተበትነዋል::
19 ቍስልህን ሊፈውስ የሚችል የለም፤
ስብራትህም ለሞት የሚያደርስ ነው፤
ስለ አንተ የሰማ ሁሉ፣
በውድቀትህ ደስ ብሎት ያጨበጭባል፤
ወሰን የሌለው ጭካኔህ፣
ያልነካው ማን አለና?

3፥13 ኢሳ19፥16፤ 45፥2፤ናሆ2፥6
3፥14 2ዜና32፥4፤
3፥15 2ሳሙ2፥26፤ ኢሳ27፥1፤ኤር51፥14፤ኢዩ1፥4
3፥16 ዘፀ10፥13
3፥17 ኤር51፥27
3፥18 1ነገ22፥17፤ መዝ76፥5-6፤ኢሳ 56፥10፤ኤር25፥27
3፥19 ኢዮ27፥23፤ ኢሳ37፥18፤ኤር 30፥13፤ሰቆ2፥15፤ ሚክ1፥9፤ሶፎ2፥15

ሩ18 ገዦች ማለት ነው::

*ውስጥ ይወድቃሉ፤* የነነዌ ምሽጎች በመጨረሻ በቀላሉ ይደረመሳሉ::

3፥13 *ጭፍሮችሽ ሁሉም ሴቶች ናቸው፤* ደካሞችና ወራሪውን ኀይል ሊቋቋሙት የማይችሉ ናቸው:: *መዝጊያዎቻቸውንም፤* የቅጥር በሮቹ መዝጊያዎች ናቸው::

3፥14 *ውሃ ቅጂ፤* ከበባ ከማድረግ በፊት የሚደረግ የተለመደ ዝግጅት ነው:: *መከላከያሽን አጠናክሪ፤* ምንም ማድረግ እንደማትችል ለመግለፅ የገባ ምፀት ነው (የ2፥1 ማብ ይመ)::

3፥15 *በዚያ፤* ጠንካራ ምሽጎችሽ ውስጥ ለማለት ነው:: *እሳት ይበላሻል፤* በታሪክና በሥነ ቅርስ ጥናት የተረጋገጠ ነው:: የአሦር ንጉሥ የሞተው በቤተ መንግሥቱ ላይ በነደደው እሳት ተቃጥሎ ነው::

3፥16 *ከሰማይ ከዋክብት እስኪበልጡ ድረስ የነጋዴዎችሽን ቍጥር፤* የአሦርን የአገር ውስጥንና የውጭን ንግድ ስፋት የሚያመለክት ነው:: *ምድሪቱን... አሟጠጡ፤* ነነዌ ችግር ውስጥ በገባችበት ጊዜ ነጋዴዎች የምድሪቱን ሀብት በሙሉ አሟጠጡ፣ የንግድ መስመሮችንም አጠፉ::

3፥17 *አንበጣ፤* ታላቅ መንጋ ሆነው በመምጣት በመንገዳቸው ያገኙትን ሁሉ ስለሚበሉ፣ በጥንት ቅርብ ምሥራቅ የነበሩ ገበሬዎች እጅግ ይፈሯቸው ነበር:: ድርጊታቸው በጥፋቷ ዘመን የነነዌ ሹማምንት ከፈጸሙት ብዝበዛ ጋር የሚነጻጸር ዘይቤ ነው:: *አይታወቅም፤* ስለዚህ የነነዌ ሹማምንት አድራሻቸው የት እንደ ሆነ እስከማይታወቅ ድረስ ይጠፋሉ:: እጅግ በጣም የሚገርመው ለምእተ ዓመታት ራሷ የተቀበረችበት ቦታ ሳይታወቅ ቈይቶ፣ እ.አ.አ. በ1845 ዓ.ም. የሥነ ቅርስ ተመራማሪዎች በመጨረሻ ስፍራውን ፈልገው ማግኘታቸው ነው::

3፥18 *ንጉሥ ሆይ፤* ነነዌ ልትወድቅ ስትል ንጉሥ የነበረው ሲን ሻር ኢሽኩን ነበር፤ ስለዚህ እነዚህ ቃሎች በትንቢት መልክ እርሱን የሚያመለክቱ ናቸው:: *እረኞችህ፤* መሪዎችን ማለት ነው:: *ዐርፈው ተኙ፤* ሞቱ ማለት ነው:: *ሕዝብህ...ተበትነዋል፤* ከጥንት ዘመን ጀምሮ ጥፋት በሚደርስበት ጊዜ የተለመደው የስደተኞች ፍልሰት በነነዌም ተከሥቶአል::

3፥19 *ስብራትህ ለሞት ያደርሳል፤* እንደ ገና ልትሠራ እስከማትችል ድረስ ነነዌ ፈጽማ ተደመሰሰች፤ ከጥቂት መቶ ዓመታት በኋላም ነፋስ ባመጣው አሸዋ ተሸፍና ተቀበረች:: ስለዚህ ታላቋ ከተማ (የዮና1፥2 ይመ፤ ከ3፥2 ጋር ያነጻጽሩ)፣ በነቢዩ በናሆም በኩል የተነገረው የእግዚአብሔር ቃል ይፈጸም ዘንድ እንደ ገና ሳትነሣ በ612 ዓ.ቅ.ክ ወደመች::